የገንዘብ እገዛ ማመልከቻው፣ የገንዘብ እገዛ ፖሊሲው፣ የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲው ነጻ ቅጂዎች በኢንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ እና የገንዘብ ድጋፍ ፒሊሲው ላይ የተገለጹት መስፈርቶች በሚያሟሉ ሌሎች ቋንቋ ዎች ማግኘት ይቻላል:

- የሆስፒታሉ የቅበላ/
  ምዝገባ ዲፓርትመንት ለማግኘት
- በ 713.338.5502 ወይም
  በ 1.800.526.2121 ይደውሉ፣ አማራጭ 5
- ማመልከቻን በፖስታ መጠየቅ:
  909 Frostwood
  Attn: PBS Financial Assistance
  Houston, TX 77024
- የማመልከቻ ቅጽን
  ከ Memorial Hermann Health System
  ድረገጽ ማውረድ: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/

**Memorial Hermann Health System**

ለገንዘባዊ ድጋፍ፣ Medicaid, Medicare, ወይም ለሌሎች ፕሮግራሞች ብቁ መሆንዎ እና አለመ ሆንዎ ለማየት፣ እንዲሁም ማመልከቻ ከማስገ ባት ጋር የተያያዘ ነጻ ሚስጢራዊ እገዛ ለማግኘት፣ የሚከተሉትን ያናግሩ:

**Patient Business Services**
909 Frostwood Dr., Suite 3:100
Houston, TX 77024
Attention: PBS Financial Assistance

ስልክ: በ 713.338.5502 ወይም
በ 1.800.526.2121 ይደውሉ፣ አማራጭ 5
ኢ-ሜይል: Patient.Billing@memorialhermann.org

አርብ: 8ኤኤም – 5ፒኤም
ሰኞ – ሀሙስ: 8ኤኤም – 7ፒኤም

የእትሙ ቀን: ህዳር 14, 2017

MEMORIAL HERMANN

4411107AMH - Amharic

# የታካሚ የገንዘብ ድጋፍ አጭር መግለጫ

## በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ



የተመለሱ ቁልፍ ጥያቄዎች:

- ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው?
- ድጋፍ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እችላለሁ?
- ማነው ለድጋፍ ብቁ የሚሆነው?
- የገቢ ገደቦቹ ምንድንናቸው?
- የገቢ ገደቦችን የማላሟላ ብሆንስ?
- የማመልከቻ ቅጽ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

MEMORIAL HERMANN

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ (FAP)

Memorial Hermann Health System ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች በገቢ፣ የቤተሰብ አባላት ብዛት እና የፌደራል ድህነት ወለል ላይ የተመሰረተ በከፊል ወይም ሙሉ ቅናሽ ለተደረገባቸው የአስቸኳይ ሕክምና ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያለው የሆስፒታል ሕክምና የገንዘብ እገዛ ያደርጋል። የገንዘብ ድጋፍ የሚፈልጉ ታካሚዎች በዚህ ሰነድ ላይ ወደ ተጠቀሰው ፕሮግራም ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

## ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው?

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው (FAP) ሽፋን የሚያገኙት አስቸኳይ ሕክምና እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው Memorial Hermann Hospital ላይ የሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች ናቸው።

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው የማይሸፍናቸው: Memorial Hermann Hospital ላይ በሚያክሙዋቹ የሆስፒታሉ ተቀጣሪ ያልሆኑ ሐኪሞች ወይም ሌሎች አቅራቢዎች ወይም ለሰጡዋቸህ አገልግሎቶች ከሆስፒታል በተለየ ሁኔታ ክፍያቸውን በሚሰበስቡ አቅራቢዎች የሚሰጡዋቹ የውበት ቀዶጥገና ሕክምናዎች።

## እንዴት ማመልከት ይቻላል

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው እና ማመልከቻ ቅጹ በአካል፣ በፖስታ፣ በስልክ እና ከ Memorial Hermann ድረገጽ መውሰድ ይቻላል። ማመልከቻውን ይሙሉ፣ የተጠየቁዋቸው ሰነዶችን ያካትቱ እና ለሆስፒታሉ የቅበላ/ምዝገባ ዲፓርትመንት ወይም የዚህ ብሮሸር ጀርባ ላይ ወደ ተጠቀሱት አድራሻዎች ያስረክቡ።

## የገቢ ገደቦች

ብቁ ለመሆን ማሟላት ከሚገባዎ መስፈርቶች አንዱ ከታች ባለው ሰንጠረዥ የተዘረዘረው የገቢ መጠን ነው:

**2018 የድህነት መመሪያዎች**

| ቤተሰቡ/ቤቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች | ገቢ በአመት |
|---|---|
| 1 | $ 12,140 |
| 2 | $ 16,460 |
| 3 | $ 20,780 |
| 4 | $ 25,100 |
| 5 | $ 29,420 |
| 6 | $ 33,740 |
| 7 | $ 38,060 |
| 8 | $ 42,380 |

ከ 8 አባላት በላይ ላሉዋቸው ቤተሰቦች/ቤቶች:
ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ሰው $4,320 ያክሉ።

## ማነው ለገንዘብ ድጋፉ ብቁ የሚሆነው?

የገንዘብ ድጋፍ መጠኑ የእርስዎ ገቢ መጠን፣ የቤተሰብ አባላትዎ ብዛት እና የፌደራል ድህነት ወለል ላይ የተመሰረተ ነው። ከፌደራል የድህነት ወለሉ አንጻር ሲታይ 200% ወይም ያነሰ ገቢ ያለው ቤተሰብ ለ 100% ቅናሽ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከፌደራል የድህነት ወለሉ አንጻር ሲታይ ከ 200% በላይ ገቢ ያለው ቤተሰብ ለቅናሽ ብቁ ሊሆን ይችላል።

ለዝርዝር መረጃ የሚከተለው ድረገጽ ላይ የሚገኘው ፖሊሲ ይዩ:
**http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/**

የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች ለአስቸኳይ ሕክምና ወይም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች የሚጠየቁት የክፍያ መጠን መድህን ያላቸው ሰዎች ከሚከፍሉት አጠቃላይ ክፍያ (AGB) የማይበልጥ ይሆናል።

የሚከተሉት ፎቶግራፍ የያዙ የማንነት ማረጋገጫዎች ተቀባይነት አላቸው:

- በግዛቱ መንግስት የተሰጠ መንጃ ፈቃድ ወይም የማንነት መለያ ካርድ
- የተማሪ መለያ ካርድ
- ፓስፖርት (የዩኤስ ወይም የውጪ)
- የዩኤስ ስደተኛ ሰነድ
- በውጪ ቆንስላ የተዘጋጀ የማንነት መለያ ካርድ
- ክሬዲት ካርድ (ፎቶግራፍ ያለው)